የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ–የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 20
ADDIS ABABA - 20th Feb., 1998

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፱/፲፱፻፺ ዓ·ም·
የጉማሮ ሻይ ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................................ ገጽ ፮፻፹፯

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 29/1998
Gumaro Tea Development Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations ............ Page 687

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፱/፲፱፻፺
### የጉማሮ ሻይ ልማት ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ሀ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩· <u>አጭር ርእስ</u>

ይህ ደንብ "የጉማሮ ሻይ ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፱/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>መቋቋም</u>

፩· የጉማሮ ሻይ ልማት ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ/ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪· ድርጅቱ፡ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 29/1998

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE GUMARO TEA DEVELOPMENT ENTERPRISE

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Gumaro Tea Development Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 29/1998."

2. *Establishment*

1) There is hereby establsihed the Gumaro Tea Development Enterprise (hereinafter 'the Enterprise') as a public enterprise.
2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

፫. <u>ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን</u>

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በጉማሮ ይሆናል። እንዳስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩. የሻይ ተክል ልማት ማካሄድ፤

፪. የሻይ ቅጠልን በመጀመሪያ ደረጃ ማዘጋጀት፤

፫. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ተዛማጅ ሥራዎችን ማካሄድ።

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፳፮ ሚሊዮን ፫፻፸፪ሺ (ሃያ ስድስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰባ ሁለት ሺህ ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፲፫ ሚሊዮን ፩፻፹፮ሺ ፬፻፺ (አሥራ ሦስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት ሺህ አራት መቶ ዘጠና ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፡ የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Supervising Authority*

A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in gumaro and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Enterprise is established are:

1) to engage in the development of tea plantations;
2) to engage in the preliminary processing of tea;
3) to engage in any other related activities conducive to the attainment of its objectives.

6. *Capital*

The authorized Capital of the Enterprise is Birr 26,372,000 (twenty six million three hundred seventy two thousand Birr) of which Birr 13,186,490 (thirteen million one hundred eighty six thousand four hundred ninety Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be held liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 20th day of February, 1998.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE